## በምረቃ ጉዞ ላይ

# 2030 ተመራቂዎች

### ዘጠነኛ ክፍል የመጀመሪያ ዓመት፡- 2026–2027

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመመረቂያ መስፈርት በጨረፍታ

**የሜሪላንድ ስቴት 1 ዲፕሎማ የሚሰጠው**ለሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምሩቃን ሲሆን፣ ይኼውም አራት መስፈርቶችን በተሳካ ሁኔታ በማሟላት ላይ የተመሠረተ ነው። እነዚህም፡- ምዝገባ፣ የኮርስ ክሬዲት፣ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) እና የሜሪላንድ የምረቃ መመዘኛዎችን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ናቸው። ተማሪዎች የመመዝገቢያ መስፈርቱን ለማሟላት ከ 8ኛ ክፍል በኋላ የአራት አመት ትምህርታቸውን በተገቢ መንገድ ማጠናቀቅ አለባቸው።ይሄ የማያስፈልግ ከሆነ አማራጭ የምዝገባ ዕቅድ ተዘጋጅቶ "ደንብ ISB-RA" ላይ በተገለፀው መሰረት ገደቡ እንዲነሳ ከተፈቀደ ብቻ ነው። ሌሎች ተፈላጊ መስፈርቶች በሙሉ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ባጭሩ ተገልፀዋል። እባክዎን ስለ 2026–2027 MCPS የኮርስ ዝርዝር/ካታሎግ ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/course-catalog/ ወይም የበለጠ መረጃ ለማግኘት የትምህርት ቤቱን ካውንስለር ያነጋግሩ።

| የኮርስ ክሬዲቶች | |
|---|---|
| የኮምፒውተር ሳይንስ፣ ኢንጅነሪንግ ወይም የቴክኖሎጅ ትምህርት (TE) | 1 ክሬዲት ያለው TE. ይህንን መስፈርት የሚያሟሉ ኮርሶች በኮርስ ዝርዝር/ካታሎግ ውስጥ የተገለጹ ሲሆን የኮምፒዩተሮችን እና የአልጎሪዝም ጥናት ወይም እውቀትን፣ መሣሪያዎችን፣ እና ክህሎቶችን በተግባር ችግሮችን ለመፍታት የተነደፉ ናቸው። |
| እንግሊዘኛ | 4 ክሬዲቶች በሥነ ጽሑፍ እና በመረጃ አጻጻፍ፣ መጻፍ፣ ንግግር እና ማዳመጥ፣ ቋንቋ እና ንባብን በተደራጀ መልኩ መማር፣ ከእነዚህ ውስጥ 1 ክሬዲት ከሜሪላንድ አጠቃላይ (MCA) የእንግሊዝኛ ምዘና ጋር የተሳለጠ መሆን አለበት። |
| ስነ ጥበብ | 1 ክሬዲት ዳንስ፣ የሚድያ አርት፣ ሙዚቃ፣ ቲያትር፣ ወይም ቪዡዋል አርት፣ ወይም እነዚህን በማጣመር። |
| የጤና ጥበቃ ትምህርት | 1 ክሬዲት፣ ኦነርስ የጤና ትምህርት A/B |
| ሂሳብ | 4 ክሬዲቶች ፣ በአልጀብራ ትምህርት 1 የሚያካትተው MCA በአልጀብራ ከሚሰጠው ትምህርት ጋር መጣጣም አለበት ወይም 1 ወይም ከዚያ በላይ ክሬዲቶች በተከታታይ በሚወሰድ የሂሳብ ኮርሶች አልጀብራ 1 እንደ ቅድመሁኔታ መሟላት አለበት፣ እና ከጂኦሜትሪ 1 ይዘት ጋር የሚሠላ ነው።<br>2018 እና ከዚያ በኋላ ለሚመረቁ ተማሪዎች የስቴት መስፈርቶች። 2018 እና ከዚያ በኋላ የሚመረቁ ተማሪዎች በያንዳንዱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዓመት የሂሳብ ኮርስ መውሰድ አለባቸው። ይህ ለተማሪዎች መመረቂያ በሂሳብ ትምህርት ከ 4 ክሬዲቶች በላይ ሊያስገኝላቸው ይችላል። |
| የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት | 1 ክሬዲት |
| ሳይንስ | 3 ክሬዲቶች ደረጃውን የጠበቀ የቀጣይ ትውልድ ሳይንስ/ Next Generation Science Standards (NGSS)፣ በስነ ህይወት ሳይንስ የሜሪላንድ የተቀናጀ ሳይንስ ምዘና (MISA) ጋር የተሣለጠ 1 የስነ ህይወት ሳይንስ ክሬዲት፣1 ፊዚካል ሳይንስ ክሬዲት፣ እና 1 ክሬዲት በየብስ/መሬት/የጠፈር ሳይንስ ወይም NGSS ኮርስ ጋር የተቀናጀ የብስ/የምድር/የጠፈር ሳይንስ ኮርስ። |
| የማህበረሰብ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ | 3 ክሬዲቶች፣ 1 ክሬዲት ዩ.ኤስ ታሪክ፣ 1 ክሬዲት የአለም ታሪክ፣ እና 1 ናሽናል፣ ስቴት፣ እና MCA ስነ መንግስት ከሚሰጠው ትምህርት ጋር የተቀናጀ የአካባቢ ስነ-መንግስት ክሬዲት መሆን አለበት። |
| የአለም ቋንቋዎች (WORLD LANGUAGES) ትምህርት እና በምርጫ የሚወሰድ (ELECTIVES) ፕሮግራም | 2 ክሬዲቶች በተመሳሳይ የአለም ቋንቋ መገኘት ያለበት ሆኖ፡-ይሄውም 2 ክሬዲቶች በአሜሪካ የምልክት ቋንቋ እና 2 ክሬዲቶች በምርጫ የሚወሰዱ (elective) ኮርሶች፣<br>**ወይም**<br>በስቴት የጸደቀ የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት (CTE) ፕሮግራም (POS) ማጠናቀቅ እናቢያንስ 0.5 ክሬዲት POS ላይ በመመስረት በተመረጡ ኮርሶች ወይም ከዚያ በላይ የተገኘ። |

| የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) | |
|---|---|
| የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) | 75 የአገልግሎት-ትምህርት ሰአታት<br>ከ 6ኛ ክፍል በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ MCPS ለሚገቡ ተማሪዎች SSL መስፈርት በተመጣጣኝ ይያዛል። |

| የሜሪላንድ አጠቃላይ ምዘና (MCA) መስፈርቶች[1፣2]<br>እነዚህ የምዘና መስፈርቶች በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) አማካይነት ሊለወጡ ይችላሉ። | |
|---|---|
| አልጀብራ 1 | በአልጀብራ 1 የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• በሴሚስተር B ኮርስ መጨረሻ ላይ አልጀብራ 1 ምዘና መውሰድ። |
| እንግሊዝኛ 10 | እንግሊዝኛ 10 ወይም ተመጣጣኝ በሆነ ኮርስ የተገኘ ክሬዲት፣ ወይም እንግሊዝኛ 10 ELs የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• ሴሚስተር B ኮርስ መጨረሻ ላይ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተርሲ ምዘና መውሰድ። |
| ስነ መንግስት | ብሔራዊ፣ ስቴት፣ እና የአካባቢ የመንግስት አስተዳደር ወይም ተመጣጣኝ በሆነ ኮርስ የተገኘ ክሬዲት እና<br>• ሴሚስተር B ኮርስ መጨረሻ ላይ ስነመንግስት መጨረሻ ኮርስ (EOC) ምዘና መውሰድ። EOC የብሔራዊ፣ የስቴት እና የአካባቢያዊ (NSL) ስነመንግስት ሴሚስተር B 20% ይይዛል። AP ስነ መንግስት ተማሪዎች AP ስነ መንግስት ፈተና ወይም MCAP ስነ መንግስት EOC ምዘና መውሰድ አለባቸው። |
| ሳይንስ | በባዮሎጂ ወይም በሌላ ተመጣጣኝ ኮርስ የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• ሴሚስተር B ኮርስ መጨረሻ ላይ የስነ ህይወት ሳይንስ የመጨረሻ ኮርስ (EOC) ምዘና መውሰድ። EOC ባዮሎጂ ሴሚስተር B ውጤት 20% ይይዛል። AP ባዮሎጂ ተማሪዎች የባዮሎጂ EOC ምዘና መውሰድ አለባቸው። |

[1]የማሟያ ፈተና፡- በተለዋጭ ፈተናዎች (AP/IB) ላይ የማለፊያ ውጤት የሚያገኙ ተማሪዎች በዚህ የትምህርት ይዘት MCA መስፈርት ያሟላሉ።
[2]ክሬዲት ማዛወር፡- ከሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ ውጪ ቀይረው የሚመጡ ተማሪዎች አንዳንድ MCA ትምህርት መስፈርቶችን በዝውውር ክሬዲት ለማሟላት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

0609.26 • EGPS